# ትምህርት 8

1. እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለመላእክት ወይም ለሰይጣንና ለአጋንንቱ ነው?

ሀ- አይደለም።

2. ታዲያ እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለማን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር ምድርን ያዘጋጀው ለእኛ ለሰዎች ነው።

3. እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ምንድን ነው?

ሀ- ሰው ነው።

4. እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረት ሁሉ ሰዎች እጅግ አስፈላጊዎች በመሆናቸው፥ እግዚአብሔር ሰውን እንዴት አድርጎ ለመፍጠር ወሰነ?

ሀ- እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ለመፍጠር ወሰነ።

5. ከሰዎች አካል የትኛው ክፍል ነው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረው?

ሀ- አእምሮአችን ስሜታችንና ፈቃዳችን ነው።

6. እግዚአብሔር በአእምሮአችን ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?

ሀ- እግዚአብሔር በአእምሮአችን መልካሙን ሁሉ እንድናስብ ይፈልጋል።

ለ- እግዚአብሔር ስለ እርሱ እንድናስብ ይፈልጋል።

7. እግዚአብሔር ስሜት የሰጠን ለምንድን ነው?

ሀ- እርሱን እንድንወደው ነው።

8. እግዚአብሔር በፈቃዳችን ምን እንድናደርግበት ይፈልጋል?

ሀ- እግዚአብሔር በፈቃዳችን መልካሙን እንድንመርጥ ይፈልጋል።

ለ- እግዚአብሔር እርሱን እንድንመርጥ ይፈልጋል።

9. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ስንት ሰዎችን ፈጠረ?
ሀ- አንድ ወንድና አንዲት ሴት ብቻ ፈጠረ።

10. የመጀመሪያው ሰው ስም ማን ነበር?
ሀ- አዳም።

11. እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረው በኋላ ምን ስልጣን ሰጠው?
ሀ- እግዚአብሔር አዳምን በምድር ሁሉ ላይ አለቃ አደረገው።

12. በመጀመሪያ በዓለም ላይ የሰው ሕይወት ምን ይመስል ነበር?
ሀ-በመጀመሪያ ቁጣ አልነበረም።
ለ- በመጀመሪያ ጥላቻ አልነበረም።
ሐ- በመጀመሪያ ክፉ ነገር አልነበረም።
መ- በመጀመሪያ ሞት አልነበረም።

13. እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ዓለም በፈጠረበት ጊዜ ይመለከቱ የነበሩት እነማን ናቸው?
ሀ-የእግዚአብሔር መላእክት ሰይጣንና አጋንንቱ ናቸው።

14. እግዚአብሔር ፍጹም የሆነውን ዓለም በመፍጠሩ ሰይጣንና አጋንንቱ ተደስተው ነበር?
ለ- አልተደሰቱም።

- እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን የመፍጠር ሥራውን ፈጽሟል?

- አዎን።

ዘፍጥረት 2፡1

1-የሰማያትና የምድር፣ በውስጣቸውም ያሉት ሁሉ አፈጣጠር በዚህ ሁኔታ ተከናወነ።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች መፍጠሩን ፈጸመ።

- እግዚአብሔር ሊሠራ ያቀዳቸውን ነገሮች ሁሉ ፈጸመ።

- አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ሥራ ይጀምሩና ሳይፈጽሙት ይቀራሉ።
- አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ቤት ማነጽ ይጀምሩና ሳይፈጽሙት ይቀራሉ።

- አንዳንድ ጊዜ ሴቶች ማሠሮ መሥራት ይጀምሩና ሳይፈጽሙት ይቀራሉ።

- ሰዎች ሥራቸውን የማይፈጽሙት፤ ሥራው በጣም ስለሚከብዳቸው ሊሆን ይችላል።

- ሰዎች ሥራቸውን የማይፈጽሙት ሌሎች ሰዎች ስለሚያስቆሟቸው ሊሆን ይችላል።

- ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እንደ ሰው አይደለም።

- ሥራው ከባድ ስለሆነ እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ አያቆምም።

- ሰዎች ከልክለውት እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ አያቆምም።

- እግዚአብሔር ሥራውን ከጀመረ ሳይፈመው አይተውም።
- እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ሁል ጊዜም የሚፈጽመው እንዴት ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈጽሞ የማይለወጥ ስለሆነ ነው።

- እግዚአብሔር ሥራውን እንዳይፈጽም ልከለክል የሚችል ምንም ነገር ስለሌለ ነው።

- እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ሰዎች ሊያስቆሙት ይችላሉ?
- አይችሉም።

- እግዚአብሔር የጀመረውን ሥራ ሰይጣንና አጋንንቱ ሊያስቆሙት ይችላሉ?
- አይችሉም።

- እግዚአብሔር አንድን ነገር ሊያደርግ ቃል ሲገባ ሁልጊዜም ይፈጽመዋል።

- እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ በኋላ ምን እንደ ሠራ እንመልከት።

ዘፍጥረት 2፥2-3

2- እግዚአብሔር ይሠራ የነበረውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ላይ ፈጽሞ ነበር፤ ስለዚህ ከሠራው ሥራ ሁሉ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ።
3- እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከው፤ ቀደሰውም፤ ካከናወነው የመፍጠር ሥራው ሁሉ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ነውና።

- እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ለምን አረፈ?

- እግዚአብሔር ደክሞት ነበር?
- አልደከመውም።

- ሁሉንም ነገሮች ከፈጠረ በኋላ እግዚአብሔር እንዴት አልደከመውም?
- እግዚአብሔር አይደክምም።

- የእግዚአብሔር ኃይል ማብቂያ የሌለው በመሆኑ።

- ታዲያ እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ለምን ዐረፈ?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ያቀዳቸውን ነገሮች ሁሉ ፈጥሮ ስለ ፈጸመ ነው።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች በስንት ቀን ውስጥ ፈጠረ?
- በስድስት ቀን።

- አንድን ቤት ለመሥራት ስንት ቀን ይፈጃል?
- ምናልባት ከሦስት ወር በላይ ይፈጃል።

- ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገሮች በስድስት ቀን ውስጥ ፈጠረ።

- ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀን ውስጥ መፍጠር የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ዘፍጥረት 2፡4ለ ና 6

4- እግዚአብሔር አምላክ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ጊዜ...
6- ውሃ ከመሬት እየመነጨ የምድርን ገጽ ያረሰርስ ነበር...

- እግዚአብሔር ምድርን በመጀመሪያ ሲፈጥር ዝናብ አልነበረም።

- በመጀመሪያ ዝናብ ካልነበረ እግዚአብሔር ምድርን በምን ያጠጣ ነበር?

- እግዚአብሔር ምድርን ያጠጣ የነበረው ከመሬት በሚመነጭ ውሃ ነበር።
ዘፍጥረት 2፡8

8- እግዚአብሔር አምላክ በምሥራቅ፣ በዔድን የአትክልት ስፍራ አዘጋጀ። ያበጀውንም ሰው በዚያ አኖረው።

- በመጀመሪያ እግዚአብሔር የምታምር ገነት ተከለ።

- እግዚአብሔር የተከላት ገነት ምን ትባል ነበረ?
- የዔድን ገነት።

- እግዚአብሔር የዔድን ገነትን የተከለው ለማን ነበር?
- ለአዳም።

- እግዚአብሔር ለአዳም ገነት የተከለው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምን እጅግ ስለሚወደው ነው።

- እግዚአብሔር በተከለው ገነት ውስጥ አዳምን አኖረው።

- እግዚአብሔር አዳምን «በገነት ውስጥ ላስቀምጥህ?» ብሎ ጠየቀው?
- አልጠየቀውም።

- እግዚአብሔር አዳምን «በገነት ውስጥ ላስቀምጥህ?» ብሎ ያልጠየቀው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም አዳምን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው አዳም የእግዚአብሔር ነው።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለ ፈጠረ ሁሉም ሰው የማን ነው?
- ሁሉም ሰው የእግዚአብሔር ነው።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ስለ ፈጠረ ሁሉም ነገር የማን ነው?
- ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ነው።

- በገነት መካከል እግዚአብሔር ሁለት ልዩ ዛፎችን ተከለ።

ዘፍጥረት 2፡9

9- በአትክልቱ ቦታ መካከልም የሕይወት ዛፍ ነበረ፤ እንዲሁም መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለው የዕውቀት ዛፍ ነበረ።

- በዔድን ገነት መካከል እግዚአብሔር የተከለው የመጀመሪያው ዛፍ ምን ይባል ነበር?

- የሕይወት ዛፍ።

- እግዚአብሔር በዔድን ገነት መካከል የሕይወትን ዛፍ የተከለው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር አዳም ከዛፉ በልቶ ለዘላለም እንዲኖር ፈልጎ ነበር።
- እግዚአብሔር አዳም የሕይወትን ዛፍ እንዲበላ አላስገደደውም።

- እግዚአብሔር አዳም እንዲመርጥ ፈለገ።

- እግዚአብሔር አዳም ከሕይወት ዛፍ መብላትን እንዲመርጥ ፈለገ።
- እግዚአብሔር አዳም ሕይወትን እንዲመርጥ ፈለገ።

- እግዚአብሔር በዔድን ገነት መካከል የተከለው ሁለተኛው ዛፍ ምን ይባል ነበር?

- መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችል የዕውቀት ዛፍ ነበር።

- መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለውን የዕውቀት ዛፍ በተመለከተ እግዚአብሔር ለአዳም አንድ ትእዛዝ ሰጠው።

ዘፍጥረት 2፡16-17ሀ

16- እግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዲህ በማለት አዘዘው፤ «በአትክልት ስፍራው ውስጥ ከሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ፍሬ ትበላለህ።
17- ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ አትብላ» [አለው።]

- መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለውን የእውቀት ዛፍ በተመለከት እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ትእዛዝ ምን ነበር?

- እግዚአብሔር አዳም የዛፉን ፍሬ እንዳይበላ አዘዘው።

- እግዚአብሔር የትኛው መልካም የትኛው ደግሞ ክፉ እንደ ሆነ ያውቃል።
- እግዚአብሔር መልካም መልካም መሆኑን ክፉም ክፉ መሆኑን ያውቃል።

- በመጀመሪያ አዳም ያውቀው የነበረው፥ መልካምን ብቻ ነበር።
- በመጀመሪያ አዳም ክፉን አያውቀውም ነበር።

- መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለውን የእውቀት ዛፍ ቢበላ ምን እንደሚደርስበት እግዚአብሔር ለአዳም የነገረውን እናንብብ።

ዘፍጥረት 2፡17ለ

17- እግዚአብሔር አምላክ አዳምን እንዲህ አለው፣ «ከእርሱ በበላህ ቀን በእርግጥ ትሞታለህ። »

- አዳም መልካምና ክፉን መለየት የሚያስችለውን የእውቀት ዛፍ ከበላ ምን ይደርስበታል?

- አዳም ይሞታል።
- ሞት ምንድን ነው?

- ብዙ ሰዎች አንድ ሞት ብቻ ነው ያለው ይላሉ።
- እግዚአብሔር ሦስት አይነት ሞት መኖሩን ይናገራል።

- ሞት ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

- ከእግዚአብሔር መለየት ሞት የሆነው ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም ሕይወት ሰጭ እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ነው።

- የሁሉም ሕይወት ምንጩ እግዚአብሔር ነው።

- ሉሲፈር ኃጢአትን ሠራ ከእግዚአብሔርም ተለየ።
- አዳምም እግዚአብሔርን ካልታዘዘ ከእግዚአብሔር ይለያል።

- ሞት የነፍስ ከሥጋ መለየት ነው።

- ብዙ ሰዎች የሚያውቁት ሞት ይህን ነው።
- አዳም እግዚአብሔርን ካልታዘዘ የአዳም አካል ይሞታል።

- ሞት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለዘላለም በእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- አዳም እግዚአብሔርን ካልታዘዘ የአዳም ነፍስ ወደ ዘላለም የእሳት ባሕር ትሄዳለች።

- አዳም እግዚአብሔርን ካልታዘዘ ከእግዚአብሔር ይለያል አካሉም ይሞታል ነፍሱም ወደ ዘላለም የእሳት ባሕር ውስጥ ትጣላለች።

- እግዚአብሔር አዳምን መልካምና ክፉን ከሚያሳውቀው ዛፍ እንዳይበላ ማዘዝ የቻለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም አዳምን የሠራው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።
- አዳም የእግዚአብሔር ነው።

- አንድ ሰው መኮትኮቻ ቢሠራ የዚያ መኮትኮቻ ባለቤት የሠራው ሰው አይደለም?
- አዎን ነው።

- አንዲት ሴት ማሠሮ ብትሠራ የማሠሮው ባለቤት የሠራችዋ ሴት አይደለችም?
- አዎን ናት።

- አንድ ልጅ መጫወቻ ቢሠራ የመጫወቻው ባለቤት የሠራው ልጅ አይደለም?
- አዎን ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን ስለ ፈጠረ አዳም የእግዚአብሔር ነው።

- እግዚአብሔር አዳምን ስለ ፈጠረው እግዚአብሔር አዳምን ማዘዝ ይችላል።

- ለእግዚአብሔር አዳምን ማዘዙ መልካም ነበር?

- አዎን።

- ለእግዚአብሔር አዳምን ማዘዙ መልካም የሆነው ለምንድን ነው?
- ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአዳም ይልቅ ጠቢብ ስለሆነ ነው።

- ሽማግሌ አባት ከወጣት ልጅ ይልቅ ጠቢብ ነው?
- አዎን።

- አሮጊት እናት ከወጣት ልጃገረድ ይልቅ ጠቢብ ናት?
- አዎን።

- የሽማግሌዎችን ምክር ማድመጥ ለወጣት ወንዶች አስፈላጊ ነው?
- አዎን።

- የአሮጊቶችን ምክር ማድመጥ ለልጃገረዶች አስፈላጊ ነው?
- አዎን።

- እግዚአብሔር ከአዳም ይልቅ እጅግ ጠቢብ ስለሆነ እግዚአብሔርን ማድመጥ ለአዳም እጅግ አስፈላጊ ነው።

- እግዚአብሔር አዳም እንዲያደምጠው የፈለገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ከአዳም ይልቅ ጠቢብ ስለ ሆነ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአዳም መልካም የሆነውን ነገር ስለሚያውቅ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ለአዳም ጐጂ የሆነውን ነገር ስለሚያውቅ ነበር።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር አዳምን ሊጠብቀው ስለፈለገ ነው።

- ሽማግሌዎች ለወጣት ልጆች የትኛው መልካምና የትኛው ጎጂ እንደሆነ ያውቃሉ።

- አሮጊቶች ለወጣት ልጃገረዶች የትኛው መልካም የትኛው ጎጂ እንደሆነ ያውቃሉ።

- ለአዳም የትኛው መልካም የትኛው ጎጂ እንደ ሆነ የሚያውቀው ማን ነበር?
- እግዚአብሔር ነበር።

- ለሁሉም ሰው መልካም የሆነውን የሚያውቀው ማን ነው?
- እግዚአብሔር ነው።

- እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ያውቃል።

- እግዚአብሔር አዳም እንዲያደምጠው ይፈልግ ነበር።

- እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲያደምጠው ይፈልጋል።

- የእግዚአብሔር እውነቶች የሚገኙት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው።

- እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲጻፍ ያደረገውን ቃሉን ሁሉም ሰው እንዲያደምጠው ይፈልጋል።